የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ
FEDERAL NEGARIT GAZETTE
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፫
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፱ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 53
ADDIS ABABA 17th April, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፬/ ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ለአነስተኛ እና መካከለኛ ከተሞች ሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮግራም ከፊል ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ.......................................ገጽ ፲፩ሺ፪፻፲፪

## Content

Proclamation No.1134/2019

The Government of the Italian Republic Loan Agreement for partly financing Small and Medieum Towns Sanitation Facilities Expansion Ratification Proclamation.........................................................Page 11212

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፬/ ፪ሺ፲፩

### <u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በጣያሊን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>

ለአነስተኛ እና መካከለኛ ከተሞች ሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮግራም ከፊል ማስፈፀሚያ የሚውል ፲፯ ሚሊዮን ዩሮ (አስራ ሰባት ሚሊዮንዩሮ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል መስከረም ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

### PROCLAMATION NO.1134/2019

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMNET OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE ITALIAN REPUBLIC

**WHEREAS,** the loan agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic stipulating that the Government of the Italian Republic provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of seventeen million Euro ( EUR 17,000,000) for partly financing Small and Mediem Towns Sanitation Facilities Expansion and Improvement Programme,was signed in Addis Ababa on the 5th day of October 2018;

**WHERE AS**, the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its session held on the 5th day of April , 2019 ;

**NOW THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia,it is hereby proclaimed as follows:

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ ” ለአነስተኛ እና መካከለኛ ከተሞች ሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮግራም ከፊል ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፬/ ፪ሺ፲፩ ”ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል መስከረም ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ስልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በስምምነቱ የተገኘውን ፲፯ ሚሊዮን ዩሮ (አስራ ሰባት ሚሊዮን ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል።

**፬.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፱ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as “The Government of the Italian Republic Loan Agreement for partly financing Small and medieum Towns Sanitation Facilities Expansion Ratification Proclamation No. 1134/2019”

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan agreement signed in Addis Ababa on the 5th day of October 2018 between the Goverrment of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic is here by ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of equivalent to 17,000,000 EUR (seventeen million Euro) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of April 2019.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**